# ነገረ እግዚአብሔር (ነገረ መለኮት)

**ጥያቄ፦አምላካችን ማን ነው?**

አምላካችን እግዚአብሔር ነው።

**ጥያቄ፦ አምላካችን እግዚአብሔር ወዴት ነው?**

አምላካችን እግዚአብሔር በሰማይ ነው። አምላካችን እግዚአብሔር በሰማይም በምድርም ነው። «አሕዛብ አምላካቸው ወዴት ነው አይበሉ፤ አምላካችን እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ነው፤ በሰማይም በምድርም ነው» ሲል ነቢዩ ዳዊት አስረድቷል (መዝ. ፻፲፫/፻፲፬/ ፻፲፫፥፲(፬)-፲፫)።

**ጥያቄ፦እግዚአብሔር አምላካችን የሚገኘው በሰማይና በምድር ብቻ ነውን?**

እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ብቻ ሳይሆን፣ ከሰማይ በላይም ከምድር በታችም ይገኛል። እግዚአብሔር በሁሉም ይገኛል። እርሱ የማይገኝበት፣ እርሱ የሌለበት ቦታ የለም። «ከመንፈስ ህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦ ል (ወደ ዕመቀ ዕመቃት) ብወርድ አንተ በዚያ አለህ ፤ እንደ ንስርም የንጋት ክንፍ ብወስድና እስከ ባሕር መጨረሻም ብበር፣ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ትይዘኛለች» በማለት ነቢዩ ዳዊት ምስክርነቱን ሰጥቶአል (መዝ.፻፴፰(፻፴፱)፥ ፯-፲፩)። ንጉሥ ሰሎሞንም በበኩሉ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና በሁሉ ዘንድ የሚገኝ አምላክ መሆኑን ሲመሰክር፣ «እነሆ ሰማይና ከሰማያትም በላ ይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ (ይወስንህ ዘንድ) አይችልም» ብሎአል (፩ነገሥ.፰፥፳፯)። ራሱ እግዚአብሔር ደግሞ በኢሳይያስ አንደበት እንዲህ ብሎአል፤ «ሰማይ መንበሬ ነው፤ ምድርም የ እግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድር ነው? እነ ዚህን ሁሉ እጄ ሠርታቸዋለችና (የእጄ ሥራዎችናቸውና)፤ እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው» (ኢሳ.፷፮፥፩-፪)።

**ጥያቄ፦እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ የሚገኝ አምላክ ከሆነ፣ ታዲያ ለምን አይታይም?**

ሰዎችም ሆነ ሌሎች ፍጡራን፣ መላእክትም ጭምር በእርሱ ፈቃድ ካልሆነ፣ እግዚአብሔርን ማየት አይችሉም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እጅግ ረቂቅ አምላክ ነውና፤ ስለዚህ ፍጡራን እርሱን በባሕርዩ ሊያዩት ወይም ለዳሰሱት አይችሉም። «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም» ሲልወንጌላዊ ዮሐንስ አስተምሮአል (ዮሐ.፩፥፲፰)። ዳግመኛም ይኸው ሐዋርያ፣ «እግዚአብሔርን ማንም አላየውም» ሲል አስረድቷአል (፩ዮሐ.፬፥፲፪)።

**ጥያቄ፦እግዚአብሔርን በዓይን ካላየነው፣ በእጅም ካልዳሰስነው፣ እንዴት ልናመልከው እንችላለን? ለእርሱስ በመንፈስና በእምነት ልንስግድለት እንዴት እንችላለን?**

እግዚአብሔር ረቂቅ አምላክ ነውና በመንፈስና በእምነት ልናመልከው ይገባናል፤ ለእርሱም በመንፈስና በእምነት ልንስግድለት ይገባናል። «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚስግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊስግዱለት ያስፈልጋቸዋል» ሲልራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮ አል (ዮሐ.፬፥፳፬)። ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስም፣ሰዓታት በሚባለው ጸሎቱ፣ «እግዚአብሔር በእጅ የማይዳሰስ፣ በዓይን የማይታይ፣ የሕይወት እሳትና ረቂቅ መንፈስ ነው» ሲል አስረድቶአል።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር በዓይን የማይታይ፣ በእጅም የማይጨበጥ ረቂቅ መንፈስ ነው ከተባለ፣ህልውናውን ማለት መኖሩን በምን ልናውቅ እንችላለን?**

የፈጠራቸውን ፍጥረታት በመመልከትና የሠራቸውን ሥራዎች በማየት የእግዚአብሔርን ህልውና (መኖር) ልናውቅ እንችላለን። «ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም፣ ይትዐወቅ በፍጥረቱ፣ በሐልዮ ወበአእምሮ፤ወከመዝ ይትአመር ኀይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም»ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮአል።

ይኸውም ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው እግዚአብሔር፣ የፈጠረውን ፍጥረት በማየትና በመመልከት ህልውናው ይታወቃል፤ በዚሁ መንገድ ኀይሉና ዘለዓለማዊው ጌትነቱም ይታወቃል ማለቱ ነው (ሮሜ.፩፥፳)።

**<u>ጥያቄ</u>፦የእግዚአብሔር መኖር በፈጠራቸው ፍጥረታት ይታወቃል ማለት እንዴት ነው?**

ለምሳሌ፦ አንድ ግንበኛ ሰው ባነጸውና በገነባው ቤት አማካይነት ማንነቱ እንደሚታወቅ የተረጋገ ጠ ነው፤ ማለት ግንበኛው ሳይታይ ግንቡን በማየት ብቻ ለቤቱ ሠሪ ወይም ገንቢ እንዳለው በግል ጽ ይታወቃል። በዚሁ ዓይነት ሰማያትንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር በፈጠራቸው ፍጥረታትና በሠራቸው ሥራዎች፤ አሁንም በልዩ ልዩ ምክንያትና በተለያየ ወቅት በሚሠራቸው ሥራዎች ህል ውናው (መኖሩ) ግልጽ ሆኖ ይታወቃል። በእርግጥ ሐዋርያው እንዳለው፣ ማንኛውም ቤት የሚሠ ራውና የሚዘጋጀው ያው በሰውነው፤ ነገር ግንግንበኛውንና ለግንቡ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ ነገሮ ች የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ በዓለም ላይየሚገኙትን ፍጥረታት በማየትና ልብ ብሎ በ መመርመር፣ ለእነርሱ ፈጣሪና ሠሪ እንዳላቸው መገንዘብ አያዳግትም።

ለምሳሌ፦ ፀሐይና ጨረቃ፣ ከዋክብትም በሙሉ ሰማያትም ጭምር ፈጣሪና ሠሪ እንዳላቸው እነ ርሱ ራሳቸው ይመሰክራሉ፤ አስገኝም እንዳላቸው ያመለክታሉ። «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብ ር ይናገራሉ፤የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል» እያለ ነቢዩ ዳዊት ይመሰክራል (መዝ.፲፰ (፲፱)፥፩-፫)። አሁንም በቅን አስተሳሰብ ሆነን ነቢዩ ዳዊት ያቀረበውን ማስረጃ ተከትለን፣ ወደ ላ ይ ቀና ብለን ብንመለከት፣በብርሃንና በሙቀት የተጐናጸፈችውን ፀሐይን፣ ጨረቃንና ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ከዋክብት ልናይ እንችላለን፤ ባየን ጊዜም እነዚህ ከምድራችን እጅግ ርቀው የሚገኙ ፍጥረታት ፈጣሪና ሠሪ እንዳላቸው እንገነዘባለን። በተመሳሳይ መንገድም በምድራችን ከሚገኙት ውቅያኖሶች በአንዱ ከዳሩ ቆመን ብንመለከት፣ የተለያዩ መርከቦች በየወደቦቻቸው ቆመው ወይ ም መስመራቸውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ(ሲንሳፈፉ) ልናይ እንችላለን፤ ታዲያ እነዚያ የምናያቸው መርኮቦች ሥሪና ባለቤት እንዳላቸው ለማንኛችንም ግልጽ ሆኖ የሚታወቅ ነው። እንደዚሁም በሰ ማይ ላይ የምናያቸው ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ፈጣሪና ሠሪ (አስገኝ) እንዳላቸው ራሳቸው ይ መስክራሉ። በዚሁ መሠረት እንደ መርከቦች የምንቆጥራቸው ዓለሞች (ፕላኔቶች) ፈጣሪና ሠሪ፣ ባለቤት እንዳላቸው ሊታወቅ ይገባል። ፈጣሪያቸውና አስገኛቸው፣ ሠሪያቸውም በፍጥረቱ ህልው ናው የሚታወቀውና ከሁሉ በላይ የሆነው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል በዓይን ሳይታዩና በእጅም ሳይዳሰሱ በሚሠሩት ሥራ ብቻ መኖራቸው የተረጋገጠላቸው ፍጥረታትም እንዳሉ ሁሉም የሚያውቀው ነው። ከነርሱ ም መካከል ነፋስ አንዱ ነው። ነፋስ በዓይን ሳይታይ፣ በእጅም ሳይዳሰስ ለሰዎች የሚሰጠው አገ ልግሎት እጅግ ከፍተኛ ነው። የሚያመጣውም ጉዳት በዚያው ልክ ከባድ ነው፤ ነገር ግን ነፋስ በ ዓይን ስለማይታይ ብቻ መኖሩን ባለ መኖር ለመለወጥ አይቻልም፤ ወይም ሰላልታየ፣ እያለ የለ ም ማለት አይቻልም፤ ምክንያቱምነፋስ መኖሩ በሥራው ይረጋገጣልና፤ ሥራውም መኖሩን ይመስ ክራል። ነፋስ በባሕርዩ ከመታየትና ከመዳሰስ በላይ በመሆኑ እንደርሱ ፍጡራን በሆኑ ወገኖች ባ ይታይም፣ ተፈጥሮአዊ ግዴታውን ለማሟላት ተግባሩን ከማከናውን ምንም ጊዜም አያርፍም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኒቆዲሞስ ጋር በተነጋገረበት ወቅት፣ የነፋስን ባሕርይና አገልግሎት አ ስመልክቶ እንዲህ ብሎአል፤ «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምጹንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከ ወዴት እንደ መጣና መዴትም እንዲሄድ አታውቅም» ብሎአል (ዮሐ.፫፥፰)።

በእርግጥ ሁሉም እንደሚያውቀው፣ ነፋስ ከወዴት እንደሚመጣና ወዴት እንደሚሄድ፣ በዓይን ሊታይ የማይቻለውን በተፈጥሮአዊ ባሕርዩ እጅግ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሳ ከዓይን የማየት ባሕርይ በላይ በመሆኑ ነው። ሰለዚህ ዓይን ነፋስን ለማየትናለመመልከት ምንም ዓይነት ኃይል የለውም ማለት ነው።

እንደዚሁም ከነፋስ እጅግ በጣም ረቂቅ የሆነው እግዚአብሔር በባሕርዩ (በህላዌው) ከፍጡራን አእምሮበላይ እጅግ የራቀና የረቀቀ በመሆኑ፣ በባሕርዩ ማንም ፍጡር ሳያየው በፈጠራቸው ፍጥረታትና በሚሰራቸው ሥራዎች አማካይነት ብቻ፣ ህልውናውን ግልጽ ሆኖ ይታወቃል። ይኸውም እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ፍጥረታት በማየትና በመመልከት የፍጥረታቱ ፈጣሪና ሥሪ እንደ ነበርና እንዳለ መረዳት እንችላለን። ይህንን አስመልክቶ ከክርስቶስ ልደት ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የነበረው ጻድቁ ኢዮብ እንዲህ ብሎአል፦ «አሁን ግን እንሰሶችን ጠይቅ ያስተምሩሃልም፤ የሰማይ ወፎችን ጠይቅ ይነግሩሃል፤ ወይም በምድር ተናገር እርስዋም ታስተምርሃለች፤ የባሕር ዓሦችም ይነግሩሃል፤ የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ» (ኢዮብ.፲፪፥፯-፱)።

ጻድቁ ኢዮብ እንዳለው በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት ብንመለከት እነርሱን ማን እንደ ፈጠራቸውና ማን እንደ ሠራቸው ልብ ብለን ብንመራመር ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልንረዳ እንችላለን።

**<u>ጥያቄ</u>፦የእግዚአብሔር ህልውና (መኖር) በፈጠራቸው ፍጥረታት ይታወቃል ከተባለ፣ እርሱ የፈጠራቸው ፍጥረታት ምንና ምን ናቸው?**

ሰማያትንና በሰማይት የሚገኙትን፣ ምድርና በምድር የሚገኙትን ፍጥረታት ሁሉ፣ ባሕርንና በባሕር ውስጥ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህ ነቢዩ ሙሴ፣ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ሲል አስረድቶአል (ዘፍ.፩፥፩)። ነቢዩ ዳዊትም፣ «ሰማይንና ምድርን የሥራ እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ» ብሎአል (መዝ.፻፴፬(፻፴፫)፥፫)። እንደገናም ይህ ነቢይ፣ «ተስፋው በአምላኩ በእግዚብሔር የሆነው ሰው ቡሩክ (ብፁዕ) ነው፤ እርሱም ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በእነርሱ ያለውንም ሁሉ የፈጠረ .... ነው» ብሎአል (መዝ.፻፵፮(፻፵፭)፥፭-፮)።

ቀጥሎም ይኸው ነቢይ፣ «ሰማያትን በጥበቡ የሠራ፣ ምህረቱ ለዘላለም ነውና፣ ለጨረቃና ለከዋክብት ሌሊትን ያስገዛቸው፣ ምህረቱ ለዘላለም ነውና»ሲል አስረድቶአል (መዝ.፻፴፭(፻፴፮)፥፭-፲)።ጻድቁ ኢዮብም፣ «ምድሪቱን ብቻዋን አንዳች አልባ (ያለምንም ድጋፍ) ያንጠለጠላት እግዚአብሔር ነው» ይላል (ኢዮብ.፳፮፥፯)።

ነቢዩ ኢሳይያስም፣ ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ይመስክራል፣ «ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያጸና፣ በእርስዋ ላይ የሚኖር ሕዝብ እስትንፋስ የሚስጥ አምላክ እግዚአብሔር ነው» ብሎአል (ኢሳ.፵፪፥፭-፯)።

ዕዝራ ነህምያም እንዲህ ሲል መስክሮአል፤ «አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ፤ ሰማይንና የሰማያት ሰማይን፣ ሠራዊታቸውንም ሁሉ፣ ምድርንና በእርስዋ ላይ ያሉትን ሁሉ ፈጥረሃል፤ ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል፤ የሰማይም ሰራዊት ላንተ ይስግዳሉ» (ነህ.፱፥፮-፳)።

ቅዱሳን ሐዋርያት ደግሞ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲጸልዩ፣«ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ስማይንና ምድርን ባሕሩንም በእርሱ የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ...»ብለዋል (የሐዋ.፬፥፳፬)።

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊም በአስደናቂ ራእዩ፣ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን እንዲህ እያሉ ማመስገናቸውን አስረድቶናል፤ «ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃል፤ ባንተ ፈቃድም ሆነዋልናተፈጥረዋልም፤ ስለዚህ ክብር፣ ውዳሴ፣ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል» (ራእይ.፬፥፲፩)።

**ጥያቄ፦እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከምን ፈጠራቸው?**

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ካለ መኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠራቸው፤ማለት «እም ኀበ አልቦ»«ኀበ ቦ» ፈጠራቸው፤ ፈጣሪ እንደ መሆኑ፣ ካለመኖር ፈጠራቸው። «ሰማያትንና ምድርን፣ ሌሎቹን በዙሪያችን የምናያቸውን ፍጥረታት እግዚአብሔር ካለመኖር (እም ኀበ አልቦ) እንደ ፈጠራቸው ታውቃለህ» ተብሎ ተጽፎአል (ቀዳማዊ መቃብያን.፯፥፳፰)።

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በሮም፣ «ካህን ወነቢይ» እየተባለ ይጠራ የነበረው ሔርማ፣ «ኖላዊ» የተባለው መምህርም፣ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ካለመኖር (እም ኀበ አልቦ) እንደ ፈጠራቸው መስክሮአል (መጽሐፈ ሔርማን ኖላዊ ክፍል 2)።

**ጥያቄ፦እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ከለመኖር (እም ኀበ አልቦ) አምጥቶ ፈጠራቸው ማለት ምን ማለት ነው?**

እግዚአብሔር ሰማያትን ምድርን ካለመኖር (እም ኀበ አልቦ) ፈጠራቸው ማለት፣ ከሌላ ነገር በማዳቀል፣ ወይም በመቁረስ፣ ወይም በማባዛት ሳይሆን፣ እንደዚሁ በመለኮታዊ ችሎታው ካለመኖር ፈጠራቸው ማለት ነው። ይኸም ችሎታ (ጥበብ) በእግዚአብሔር እንጂ በፍጡራን ዘንድ አይገኝም።

ማንኛውም ብልኀተኛ ሰው ለመሥራት የፈለገውን ዕቃ የሚሠራው እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ከአንድ ነገር ከፍሎ፣ ወይም ቆንጥሮ በመውሰድ ነው። እግዚአብሔር ግን ምንም ነገር ለማድረግ አይሳነውምና የመጀመሪያዎቹን ፍጥረታት የፈጠረው ካለመኖር (እም ኀበ አልቦ) ነው። «በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?» ሲል የእግዚአብሔር ቃል የሚያስረዳው ስለዚህ ነው (ዘፍ.፲፰፥፲፬)። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ለድንግል ማርያም ምጽአተ ወልደ እግዚአብሔርን ሲያበሥራት፣ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» ሲል አስረድቶአታል (ሉቃ.፩፥፴፯)።

አርጌንስና ሌሎች የተሳሳተ ግምት የነበራቸው ሰዎች ግን፣ «እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ዘለዓለማዊት ከሆነች ቁስ አካል (ማተር) ፈጠራቸው» ሲሉ አስተምረዋል። (ኦር.ዲ.ፕሪንሲፕል )። ነገር ግን የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሰማያትና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት ከራሱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ ምንም ነገር እንዳልነበረ ታስተምራለች፤ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ዘለዓለማዊ የሆነ ነገር እንዳልነበረ ታምናለች።

**ጥያቄ፦እግዚአብሔር ካለመኖር (እም ኀበ አልቦ) የፈጠራቸው ፍጥረታት ስንት ናቸው?**

እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠራቸው ፍጥረታት ብቻ ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው፦

ሀ. ሰማያትና ምድር (የማይታዩትና የሚታዩት)
ለ. መላእክት
ሐ. ብርሃን፣ ጨለማ፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ እሳት
መ. ነፍስና ሌሎችም ናቸው።

**ጥያቄ፦የእግዚአብሔር ዘመን ስንት ነው?**

የእግዚአብሔር ዘመን ቁጥር የለውም። እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ነበረ፤ በዚህ ዘመን ግን አልነበረምአይባልም። ፍጥረታት ሁሉ መነሻና መድረሻ አላቸው። ያልነበሩበት ዘመን፣ ያልተፈጠሩበት ጊዜ ነበር። እንደዚሁም እያንዳንዱ ፍጡር ለመኖር የተወሰነለትን ጊዜ ሲጨርስ በሞት ይለያል። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ይህ ሁሉ የለም፤ ለዘለዓለም የኖረና የሚኖር እርሱ ብቻ ነው።

**ጥያቄ፦ስለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት ቅዱስ መጽሐፍ ምን ይላል?**

እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ቦታ ይመስክራል። «ተራሮች ሳይፈጠሩ፣ ምድርም፣ ዓለምም ሳይሠራ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ አንተ ነህ»

ሲል ነቢዩ ዳዊት መስክሮአል (መዝ. ፹፱(፺)፥፩-፫)። እንደገናም ይኸው ነቢይ፣ «አንተ ግን ጌታ ሆይ፤ ለዘለዓለም ትኖራለህ፤ መታሰቢያህም ለልጅ ልጅ ነው» ሲል አስረድቶአል። በግእዙ፣ «ወ ዝክርከኒ ለትውልደ ትውልድ» ይላል (መዝ.፻፩(፻፪)፥፲፪)። በተለይም ሁሉ ሲያልፍና ሲለወጥ እ ግዚአብሔር ግን ምንጊዜም የማይለወጥና የማያልፍ አምላክ መሆኑን ሲመሰክር ይኸው ነቢይ እ ንዲህ ይላል፤ «ጌታ ሆይ፤ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደልብስ ያረጃሉ፣ እንደ መጐናጸፊያም ትለው ጣቸዋለህ፤ ይለወጣሉም፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ (ምንጊዜም አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አ ያልቁም» (መዝ.፻፩(፻፪)፥፳፭-፳፯)። ጻድቁኢዮብም በበኩሉ እንዲህ ብሎአል፤ «እነሆ እግዚአ ብሔር ታላቅ ነው፤ እኛም አናውቀውም፤ የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም (አይታወቅም)» (ኢዮ ብ.፴፮፥፳፮)። ነቢዩ ኢሳይያስ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት ሲያስረዳ፣ «እግዚአብሔ ር የዘለዓለም አምላክ፤ የምድር ዳርቻ (መላዋን ምድር) ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፤ አይታክትም፤ ጥበቡም አይመረመርም» ብሎአል (ኢሳ.፵፥፳፰)።

ራሱ እግዚአብሔርም በኢሳይያስ አንደበት ዘለዓለማዊ መሆኑን ሲገልጽ፣ «ያቆብ ሆይ፤ የጠራሁ ህ እስራኤል ሆይ፤ ስማኝ፣ እኔ ነኝ፤ እኔ ፊተኛው ነኝ (ከሁሉ በፊት የነበርኩ እኔ ነኝ)፤ እኔም ኋለኛው ነኝ።እጄም ሰማያትን ዘርግታለች» ብሎአል (ኢሳ.፵፰፥፲፪-፲፫)። ለቅዱስ ዮሐንስ ወንጌ ላዊ በተገለጸበት ራእይም፣ የሰማይ መላእክት ስለ እግዚአብሔር ዘለዓለማዊነት እየመሰከሩ ሲያ መሰግኑት፣ «ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ ትልቁን ኀይልህን ስለ ያ ዝህ፣ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን» ብለዋል (ራእይ.፲፪፥፲፯)።

ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን የሞላ፣ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ እንደሆነ፣ ራሱ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አንደበት እንዲህ ይላል፤ «ሰው በስውር ቢሸሸግ፣ እኔ አላየው ምን? ሰማይንና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን?» (ኤር.፳፫፥፳፬)። ዘመን የማይቆጠርለት፣ ከ ዘለዓለም እስከዘለዓለም ሕያው ሆኖ የኖረውና የሚኖረው እግዚአብሔር፣ በሰማይና ከሰማያት በ ላይ በምድርና ከምድር በታች የሚገኝ፣ በሁሉም ምሉዕ የሆነው አምላክ፣ በዘመን ሐዲስ ለቅዱ ስ ዮሐንስ በራእይ ተገልጾ ሕያውና ዘለዓለማዊ አምላክ መሆኑን ሲያስረዳ፣ «እነሆ በቶሎ እመ ጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍልው ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፤ አልፋና ኦ ሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ብሎአል (ራእይ.፳፪፥፲፪-፲፬)።

## <u>ጥያቄ</u>፡-የአምላካችን ስሙ ማን ነው?

ሰማያትንና ምድርን ጠቅላላው ዓለም በሙሉ የፈጠረ እግዚአብሔር ሰለሆነ፣ ስሙ ፈጣሪ ይባላ ል። ከሁሉ በፊት ራሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦ፣ «እኔ ኤልሻዳይ ነኝ ሲል ነግሮታል ( ዘፍ.፲፯፥፩)። «ኤልሻዳይ» ቃሉ ዕብራይስጥ ሲሆን፣ ትርጉሙም «ሁሉን ቻይ» ማለት ሁሉን መ ድረግ የሚችል ነው። ስለዚሁም ኢዮብ እንዲህ ብሎአል፤ «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆ ንህ፣ አሳብህም ይከለክል ዘንድ ከቶ ማንም እንደማይችል አውቃለሁ» (ኢዮብ.፵፪፥፪)።

## <u>ጥያቄ</u>፡-የፈጣሪያችን ስሙ ማነው?

የፈጥሪያችን ስሙ እግዚአብሔር ነው። «እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜም ይህ ነው፤ ክብሬን ለ ሌላ ምስጋናዬንም ለጣኦት አልሰጥም» ሲል ራሱ በኢሳይያስ አንደበት ተናግሮአል (ኢሳ.፵፪፥፰) ። ለሙሴም፣ «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ፤ ለእስራኤል ልጆችም፣ ያለና የሚኖር ወደ እናንተ ላከኝ ትላቸዋለህ» ሲል ነግሮታል (ዘጸ.፫፥፲፬)።

ከዚያው አያይዞም እንዲህ ሲል ነግሮታል፤ «ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ትላቸዋለህ፤ የአባቶቻች ሁ አምላክ፣ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር ወደ እና ንተ ላከኝ፤ይህ ለዘላለሙ ስሜ ነው፤ እስከ ልጅ ልጅ ድረስም መታሰቢያዬ ይህ ነው» (ዘጸ.፫፥፲፭-፲፮)። እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ታላቅነቱን፣ ቅድስናውን፣ ፍቅሩን፣ ንጽሕናውንና ዘላለማ ዊነቱን የሚያመለክቱ እጅግ በርከት ያሉ ስሞች በቅዱስ መጽሐፍና በመጻሕፍተ ሊቃውንት ተመ ዝግበው ይገኛሉ።

**<u>ጥያቄ፦</u>ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ አንድ ብቻ ነውን?**

አዎን፤ ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት የፈጠረ አንድ አምላክ አንድ ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላክ በአምላክነቱ (በእግዚአብሔርነቱ) ዘለዓለም አንድ ብቻ ነው።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ አንድ ብቻ መሆኑን ማን ይመስክራል?**

ቅዱስ መጽሐፍና የቅዱሳን የቤተክርስቲያን አባቶች የጻፍዋቸው ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ ይመስክራሉ፤ እንዲህ ሲሉ፦ «እግዚአብሔር አምላክ አንድ እንደሆነ ታውቅ ዘንድ ይህ ላንተ ተገለጠ፤ ከእርሱምሌላ አምላክ የለም… እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ፣ በታችም በምድር አምላክ እንደሆነ ዛሬ እወቅ በልብህም ያዝ» (ዘዳ.፬፥፴፭-፴፱)።

«እስራኤል ሆይ፣ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጽም ልብህ፣ በፍጽም ነፍስህ፣ በፍጽም ኃይልህ ውደድ» (ዘዳ.፮፥፬)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ፣ «ከሁሉ በላይ የሚሆን፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር፣ የሁሉ አባት የሆነ አንድ አምላክ አለን» ሲል መስክሮአል (ኤፌ.፬፥፭-፮)። ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ አበውም በ፫፻፳፭ ዓ.ም በቀኖና ሃይማኖታቸው፣ «ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ እግዚአብሔር አብ እናምናለን» ብለዋል።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔርን በዕውቀታችን (በጥበባችን) መርምረን ልናገኘውና ልናየው እንችላለን?**

ቀደም ብለን እንደ ገለጽነው፣ እግዚአብሔር በዓይን የማይታይ፣ በእጅ የማይዳሰስ፣ በራሱ አካል ጸንቶ የሚገኝ የማይመረመር ረቂቅ መንፈስ ነው፤ ስለዚህ ከፍጡራን ወገን ማንም ቢሆን የረቀቀና የመጠቀምርምር ቢያደርግ እግዚአብሔርን ማግኘትም ሆነ ማየት በፍጹም አይችልም። እግዚአብሔር እያዩ የሚያመልኩት፤ እየዳሰሱ የሚሰግዱለት አምላክ አይደለም። የማይታይና የማይዳሰስ፣ በቦታም የሚወስንባይት እንጂ አምላክ አይደለምና። እግዚአብሔር ግን አይታይም፤ አይዳሰስም፤ አይመረመርም፤ አይወሰንም። ስለዚሁም ኢዮብ ጻድቅ እንዲህ ይላል፤ «በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የሚያስፈራ ግርማ አለ፤ ሁሉን የሚችል አምላክን እናገኝ ዘንድ አንችልም፤ በኃይል ታላቅ ነውና» (ኢዮብ.፴፯፥፳፪-፳፬)። «የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችለውን አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? እርሱ ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ?» (ኢዮብ.፲፩፥፯-፱)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፣ «እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳን አላየውም፤ ሊያየውም አይችልም፤ ለእርሱ ክብርና የዘለዓለም ኀይል ይሁን፤ አሜን» ብሎአል (፩ጢሞ.፮፥፲፮)።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር በባሕርዩ፣ በሰውም ሆነ በመላእክት አእምሮ ሊታወቅና ሊመረመር እንደማይቻል ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል፤ ስለዚሁ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ምን ብለው አስተማሩ?**

እግዚአብሔር በባሕርዩ በእምነት ዓይን ካልሆነ፣ በሥጋዊ ምርምር በምንም መንገድ የማይታይ፣የማይገኝና የማይመረመር መሆኑን በሰፊው አስተምረዋል። ለምሳሌ፦ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ማስረጃዎች እንመልከት፦ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በጸሎተ ቅዳሴው፣ «ዳርቻ የለህም፤ ያገኝህ የለም፤ የሚያገኝህምየለም። ራስህን አንተ ታውቃለህ፤ መንግሥትህም አያልቅም፤ ኀይልህም አይሻርም፤ ገናንነትህ መጨረሻየለውም፤ ኄትነትህ አይሰወርም፤ አንተ ከሁሉ የተሰወርህ ነህ፤ ሁሉ ግን ላንተ የተገለጸ ነው» ሲል አስረድቶአል (ቅዳሴ ዘወልደ ነጐድጓድ ቁ.፬፥፮)። ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያም እንዲህ ብሏል፤ «የእግዚአብሔርን የታላቅነቱን ነገር ብንተች፣ ብንመረምር፣ ድፍረት ነው፤ የማይመረመር መለኮቱን ከማወቅ ልቡናችን (አእምሮአችን) ይደክማልና አይደረስበትም፤ ሕሊና መርምሮ ሊያውቀው ያልቻለው፣ ቃል (አንደበት) ገልጦ ሊናገረው አይችልምና፤

የምናያቸውን ፍጡራን መርመሮ ማወቅ ለልቡናችን የሚረቀው ከሆነ፣ እንደሚገባቸውም እንናገር ዘንድ ካልቻልን፣ የማናውቀውን ለመናገር እንደምን እንደፍራለን?» (ባስልዮስ፣ ሃይማኖተ አበው ፣ ገጽ.፻፲ ቁ.፫-፬ ሕትመት ፲፱፻፹፮ ዓ.ም)። በተጨማሪም ይህ ቅዱስ አባት፣ «መላእክት፣ የ መላእክት አለቆች ሁሉ በየወገናቸው፣ በየነገዳቸው ከሁሉም ፍጡራን ጋር አንድ ወገን ሆነው፣ በአንድነት ቢሰበሰቡ፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ (ህልውና) ትንሽ እንኳን ያውቁ ዘንድ አይችሉም » ሲል አስረድቶአል (ባስልዮስ፣ ሃይማኖተ አበው ገጽ.፻፲፩ ቁ.፲፬)።

በ ፬፻፴፩ ዓ.ም በኤፌሶን በተደረገው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ተካፋይ የነበረው የአንቆራው (የአንካ ራው) ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎዶጦስም እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «እግዚአብሔር በሰው ኅሊና እን ደማይመረመር፣ ስለመለኮት መርምሮ አያውቀውም፤ የመለኮት ባሕርይ እንናገራለን፤ የሰው ኅሊና መለኮትን መርምሮ አያውቀውም፤ የመለኮት ባሕርይም በሰው ኅሊና ከመመርመር የራቀ ነውና፤ ከኅሊናትም (ከአእምሮ) ሁሉ ፍጹም የራቀ ነው» (ቴዎዶጦስ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ ፻፷፩)።

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስም፣ «እግዚአብሔር ለአነዋወሩ ጥንት የለውም፤ ለዘመኑም ቁጥር የ ለውም፤ለዓመታቱም ልክና ቁጥር የለውም፤ ለዓመታቱም ልክና ቁጥር የለውም ... በኅሊና የማያገ ኙት ስውር
ነው፤ በልቡናም የማይረዱት ምጡቅ ነው» ሲል አስረድቷል (ቅዳሴ ዘኤጲፋንዮስ፣ ቁ.፬-፯)። ቅ ዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ደግሞ ሰለ እግዚአብሔር ምሉእነትና ዘለዓለማዊነት ሲመሰክር፣ «ሰማያት ን የፈጠረ ይህ ነው፤ ምድርንም የፈጠረ ይህ ነው፤ ለመለኮቱ ጥንት (መሠረት) የለውም፤ ቀኝ የ ለውም፤ ግራም የለውም፤ መካከልም የለውም፤ በዓለም ዳርቻ (ከዚያም ውጭ) ሁሉ የመላ ነው እንጂ፤ ከመላእክት ሁሉኅሊና የተሰወረ ነው፤ ባሕርዩን የሚያውቀው የለም፤ በእጁ (በጥበቡ) የተ ፈጠረውንም የሚቆጥረው የለም» ብሎአል (ቅዳሴ ዘጎርጎርዮስ፣ ቁ.፩-፲፩)። ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስ ክንድርያም እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ ልቡስ ሥጋ ነው ብለው ያስተማሩትን በመቃወም፣ «ውስጣዊ ሰውነት ግን የማያረጅ ዕውቀት ያለው ነፍስ ነው፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር በሥጋ ተ ሰውሮያለ ነፍስን በቸርነቱ እግዚአብሔርን የሚመስል አድርጎ ፈጠረው። እግዚአብሔር ግን ጥን ቱን ሥጋ አይደለምና አይወሰንም፤ እርሱም እሳት ነው፤ብርሃንም ነው፤ ማንም ማን አይቀርበው ም፤ ኅሊናም መርምሮ አያገኘውም፤ አይመረመርም፤ ከላይ ሆኖስማይን ይከድናል፤ ከታችም ሆኖ ምድርን ይሸፍናል» ሲል አስረድቷል (ቄርሎስ፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ.፬፻፷፫ ቁ.፷፯)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም አምላካችን የማይመረመርና የሰው አእምሮ የማይደርስበት መሆኑን በመግለጽ እንዲህ ብሎአል፤ «...እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃ ን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳን አላየውም፤ ሊያየውም አይችልም፤ ለእርሱ ክብርና ኀይል ለዘላ ለም ይሁን አሜን»(፩ጢሞ.፮-፲፮)።

## <u>ጥያቄ፡-</u>እግዚአብሔር አምላክ ሰማያትንና በሰማያት የሚገኙትን፣ ምድርንና በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ የፈጠረ ምን ግዜ ነው?

ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩን፣ የስማያትና የምድር አፈጣጠር ቅደም ተከተል ከዚህ እ ንደሚከተለው ነው፡- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ስማይንና ምድርን ፈጠረ፤ ማለትም መጀመሪያ ስማያትንና በስማያት ላይ የሚኖሩትን፣ የሚታዮትንና የማይታዩትን ፈጠረ።

ከዚያ ቀጥሎም እግዚአብሔር ምድርንና በምድር የሚኖሩትን ፈጠረ። ሁሉንም በቃሉ ይሁኑ (ይ ፈጠሩ)እያለ በነቢብ ማለት በመናገር ፈጠራቸው። ጨለማም ከሚታዩት ፍጥረታት አንዱ ነው። ቀጥሎም እግዚአብሔር፣ «ብርሃን ይሁን» ብሎ ብርሃንን። ብርሃንም በእግዚአብሔር ቃል ተፈጠ ረ። እግዚአብሔር የፈጠረውን ብርሃን እጅግ መልካም እንደሆነ አየ፤ ብርሃኑን ከጨለማ ለየው፤ ብርሃኑን ቀን፣ ጨለማውን ሌሊት ብሎ ጠራው። ማታም ሆነ፤ ጠዋትም ሆነ፤ አንድ ቀን ተብሎ ተቆጠረ (እሁድ በግእዝ አንድ ማለት ነው፣ ዘፍ፩፥፫-፭)።

## ጥያቄ፦ከዚያስ ቀጥሎ እግዚአብሔር ምን ፈጠረ?

በመጀመሪያው ቀን የፈጠረውን ውኃ ለሁለት ከፈለው፤ ማለት ግማሹን ውኃ ወደ ላይ እንዲወጣ አዘዘው፤ ውኃውም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደ ላይ ወጣ። እግዚአብሔር ወደ ላይ የወጣውን ውኃ «ጠፈር» ይሁን ብሎ አዘዘ። ውኃውም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ «ጠፈር» ሆነ፤ እግዚአብሔር ጠፈሩን «ሰማይ» የሰማይ ጠፈር ብሎ ጠራው። ወደ ታች የቀረውን ውኃ ደግሞ በምድር እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን ቦታ ያዘ። በዚህ ጊዜ ቀን ሆነ፤ ሌሊትም ሆነ።
ጊዜውም ሁለተኛ ዕለት ተባለ። በግእዝ ሰኑይ ማለት ሁለተኛ ማለት ሲሆን፣ ስለዚህ ሰኞ ተባለ (ዘፍ.፩፥፮-፲፪)።

## ጥያቄ፦ከዚያስ በኋላ እግዚአብሔር ምን ፈጠረ?

እግዚአብሔር፣ «ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርና ቡቃያን እንደ ወገኑ፣ ዘርም ያለበትን ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ እንደየወገኑ ታብቅል» አለ። እግዚአብሔር እንዳለው ሆነ፤ ምድርም እንደ እግዚአብሔርቃል ዘር የሚሰጠውን ሳርና ቡቃያ እንደ ወገኑ፣ ዘርም ያለበትን ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ እንደየወገኑ (በያይነቱ) አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። ቀንም ሆነ፤ ሌሊትም ሆነ፣ ጊዜውም ሶስተኛ ቀን ተባለ፤ በግእዙ ሠሉስ ይላል። ሦስተኛ ማለት ነው። በአማርኛም ግን «ማክሰኞ» ይባላል (ዘፍ.፩፥፲፩-፲፫)።

## ጥያቄ፦እግዚአብሔር ከዚያ ቀጥሎ ምን ፈጠረ?

«ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናትን በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ ለምልክቶችም፣ ለዘመናትም፣ ለዕለታትም፣ ለዓመታትም መለያ ይሁኑ፤ በምድር ላይም ያበሩ ዘንድ፣ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ» ብሎ ብርሃናትን ፈጠረ። እግዚአብሔር ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን ፈጠረ፤ ትልቁ ብርሃን ( ማለት) ፀሐይ በቀን እንዲሠለጥን ማለት እንዲያበራ አደረገ። ከዋክብትም ደግሞ ፈጠረ። እግዚአብሔር በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ የፈጠራቸውን ብርሃናት በሙሉ በሰማይ ጠፈር አኖራቸው (ዘፍ.፩፥፲፬-፲፱)።

እግዚአብሔርም ይህን ያደረገውን ተመለከተ። መልካምም እንደሆነ አየ። ቀንም ሆነ፤ ሌሊትም ሆነ፤ አራተኛም ቀን ተባለ። በግእዙ «ረቡዕ» ይባላል፤ አራተኛ ማለት ነው።

## ጥያቄ፦እግዚአብሔር ከአራተኛው ቀን በኋላ ምን ፈጠረ?

እግዚአብሔር፣ «ውኃ፣ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፤ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ» ባለ ጊዜ በውኃይቱ ታላላቅ ዓሳ አንበሪዎች፣ አንደየወገኑ፣ ሕያዋን ፍጥረታት ሆነው የሚንቀሳቀሱት፣ በክንፍ የሚበሩት፣ ወፎች፣አሞሮች እንደየወገናቸው ተፈጠሩ።

እግዚአብሔር እንዚህን በውኃ ውስጥ የፈጠራቸውን ተመለከተ፤ መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ባረካቸው፤ «ብዙ ተባዙም የባሕርንም ውኃ ሙሉአት፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ አለ። ቀንም ሆነ፤ ሌሊትም ሆነ፤ አምስተኛው ቀን ሆነ።» (በግእዙ ሐሙስ አምስተኛ ማለት ነው፣ ዘፍ.፩፥፳-፳፫)።

## ጥያቄ፦ከዚያስ በኋላ እግዚአብሔር ምን ፈጠረ?

ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ የወገኑ፣ በእግር የሚሸከረከሩትን፣ በክንፍ የሚበሩትን አእዋፍንና አንስርትንእንደየወገኑ፣ እንስሳትን፣ አራዊትን፣ በጠቅላላ በየብስ ለመኖር የሚችሉትን ፍጥረታት ፈጠረ፤ያም እጅግ መልካም እንደሆነ አየ (ዘፍ.፩፥፳፬-፳፮)። በመጨረሻም እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ ሰውም በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጠረ።

## ጥያቄ፦ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዴት አድርጎ ፈጠረው?

ሰውን በመልኩና በምሳሌው ፈጠረው። ከምድር አፈር አበጀው (ሠራው)፤ በአፍጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ፍጡር ሆነ።

እግዚአብሔር አምላክ ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እንዲህም ብሎ ባረካቸው፣ «ብዙ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት፤ ግዙአትም፤የባህርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ አራዊትንም፣ እንስሳትንም ሁሉ ግዙአቸው።» ቀጥሎም እንዲህ አላቸው፤ «እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በምድር ፊት ሁሉ ላይ ዘሩበእርሱ ያለውን ሐመልማል (ለምለም) ሁሉ ሰጥቻችኋለሁ።» ለምድር አራዊት ሁሉ፣ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፣ ሕያው ነፍስ ላላቸው ለምድር ተንቀሳቃሾችም ሁሉ፣ «በምድር የሚበቅለው ሐመልማል (ለምለም) ሁሉ መብል ይሆናቸው ዘንድ ሰጥቻችዋለሁ፤ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉና ያደረገውን ሁሉ እነሆ እጅግ መልካም እንደሆነ አየ። ማታም ሆነ፤ ጥዋትም ሆነ፤ ስድስተኛ ቀን ተባለ» (ዘፍ.፩፥፳፯-፴፩)። እግዚአብሔርም በዚሁ ቀን የመፍጠር (የአስተናብሮ) ሥራውን ፈጸመ፤ ስለዚህ ቀኑ እግዚአብሔር የመፍጠር ሥራውን የፈጸመበት ስለሆነ «ዓርብ» ይባላል፤ «መካተቻ፣ መደምደሚያ» ማለት ነው።

**<u>ጥያቄ</u>፦እግዚአብሔር ከስድሰተኛው ቀን በኋላ ምን ሠራ?**

እግዚአብሔር ከስድስተኛው ቀን በኋላ ምንም አልሠራም። ለመፍጠር የፈለገውን፣ ለመሥራት ያሰበውን በሙሉ በመጀመሪያው ቀን ጀምሮ በስድስተኛው ቀን አከናውኖ ፈጽሟልና።

**<u>ጥያቄ፦</u> እግዚአብሔር በስባተኛው ቀን ምን ሠራ?**

እግዚአብሔር በስባተኛው ቀን ምንም አልሠራም። እግዚአብሔር በስድሰተኛው ቀን ሥራውን ሁሉ ስለ ፈጸመ በስባተኛው ቀን ዐረፈ። እንደዚሁም እግዚአብሔር ሥራውን ጨርሶ ያረፈበትን ስባተኛውን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም (ዘፍ.፪፥፩-፫)።

**<u>ጥያቄ</u>፦እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በመልኩና እንደ ምሳሌው ፈጠረው ማለት ምን ማለት ነው?**

እግዚአብሔር አዳምን በራሱ መልክ ፈጠረው ማለት ነው፤ ይኸውም በአእምሮና በጌትንት እርሱን አስመስሎ ፈጠረው ማለት ነው።

**<u>ጥያቄ፦</u>እግዚአብሔር አምላክ፣ «ሰውን (አዳምን) ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት» ማለት ምን ማለት ነው?**

«ከአፈር አበጅው» ማለት ከአራቱ ባሕርያት ፈጠረው ማለት ነው። «እስመ ውእቱ ለሐኮ እም አርባዕቱ ጠባይዕ ወእሙንቱ እሳት ወነፋስ፣ ማይ ወመሬት» እንዲል። አራት ባሕርያት የተባሉት እሳት፣ ነፋስ፣ ውሃ፣ መሬት ናቸው (መቅ. ወንጌል ሁለተኛ ጉባኤ)።

«በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት» ማለቱም፣ በደማዊነት ነፍሱ ላይ ነባቢትና ለባዊት ነፍስን አሳደረባት ሲል ነው። ስለዚህ የመጀመሪያው ሰው (አዳም) ባደረችበት ለባዊትና ነባቢት ነፍስ ምክንያት ከሌሎቹ ፍጥረታት ተለይቶ እዋቂና አስተዋይ፣ ባለአእምሮ ሆነ፤ የጸጋ ልጅነትንም ከእግዚአብሔር አገኘ። በዚሁም እግዚአብሔርን የሚመስል ሆነ። ስለዚህም አዳም ለባዊትና ነባቢት ነፍስ ያለው ሆኖ በመፍጠሩ፣ የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ተብሎ ተጠራ። «ወዓዲ አክበሮ በንጽሕት ነፍስ ዘይእቲ ማኅተመ ሕይወተ መንፈሳዊት፣ አንተ ባቲ አክበሮ እም ኵሉ ፍጥረታት ዘታሕተ ሰማይ» ከአራት ባሕርያት አዋህዶ ፈጠረው ብሎ ነበርና፤ ዳግመኛም በአራቱ ማእዘን ካሉ ፍጥረታት ለይቶ ባከበረበት የሥጋ ሕይወት፣ የደመ ነፍስ ሕይወት በምትሆን በነባቢት ነፍስ አከበረው። «ወትትዐወቅ በኃይለ ንባብ፣ ዛቲ አርአያ ገጹ ለእግዚአብሔር ወአም ሳሊሁ። በከመ ይቤ መጽሐፍ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ» (ዘፍ.፩፥፳፮)።

በምስጢር በመናገር ትታወቃለች፤ መጽሐፍ ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር እንዳለ፣ «ይኽቺውም የእግዚአብሔር መታወቂያና ምሳሌ ናት» (መቅ. ወንጌል ሁለተኛ ጉባኤ)።

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም ስለዚሁ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «በኦሪት የተጻፈውን ቃል ምክን ያት አድርገው ለእግዚአብሔር ቀድሞ ሥጋ እንደ ነበረው የሚናገሩ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በእኛ አምሳል እንፍጠር አለ፤በእኛ አምሳል ያለውም ስለ ሰው ሥጋ ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ ስለ ውስጣዊ ሰውነታችን ስለ ነፍሳችን ተናገረ እንጂ፤ እርሱም ሁል ጊዜ በመታደስ ጽንቶ ይኖራል» (ሃይማኖተ አበው፣ ቄርሎስ፣ ገጽ.፪፻፳፫ ቁ.፳፫፥፳፬)።

ቀጥሎም ይህ ቅዱስ አባት እንዲህ ይላል፤ «ውስጣዊ ሰውነት ግን የማይለወጥ ዕውቀት ያለው ነፍስ ነው፤ ዳግመኛም እግዚአብሔር በሥጋ ተሰውሮ ያለ ነፍስን በቸርነቱ እግዚአብሔርን የሚመስል  አድርጎፈጠረው» (ሃይማኖተ አበው ቄርሎስ፣ ገጽ.፪፻፳፫ ቁ.፳፯)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ሰው ከሥጋ፣ ከነፍስ (ደማዊት ነፍስ)፣ ከመንፈስ፣ ማለት ከለባዊነትና ከነባቢት ነፍስ እንደ ተፈጠረ ሲያስረዳ፣ «የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን፣ መንፈሳችሁንም፣ ነፍሳችሁንም፣ ሥጋችሁንም ይቀድስ» ብሎአል (፩ተሰ.፭፥፳፫)። ስለዚህ ከፍ ብለን እንደ ገለጽነው፣ ሰው ለባዊትና ነባቢት ነፍስ ሰላለችው፣ «የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ» ነው እየ ተባለ ይጠራል።

**<u>ጥያቄ</u>፤እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ከፈጠራቸው በኋላ የት አስቀመጣቸው?**

አሳምሮ አዘጋጅቶ በፈጠራት በኤደን ገነት አስቀመጣቸው። እየሠራ ይጠብቃት ዘንድ እግዚአብሔር አዳምን በገነት አስቀመጠው (ዘፍ፪፥፲፭)።

**<u>ጥያቄ፦</u> እግዚአብሔር አዳምን፣ የመጀመሪያው ሰው፣ ምን ብሎ አዘዘው?**

እግዚአብሔር አዳምን ወስዶ ያበጃትም፣ ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው፤ እንዲህም ሲል አዘዘው፤ «መልካሙንና ክፉውን ከምታስታውቀው ዛፍ (ከዕፀ በለስ) አትብላ፤ ከእርስዋ ብት በላ ግን ወዲያውኑ ሞትን ትሞታለህ» (ዘፍ.፪፥፮-፲፯)።

**<u>ጥያቄ፦</u> ሰይጣን (እባብ) ሔዋንን ምን አላት?**

«ሞትን አትሞቱም፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ፣ እንደ እግዚአብሔር መልካሙንና ክፉውን የምታውቁ እንደምትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ»ብሎ ነገራት።

**<u>ጥያቄ፦</u>ሴቲቱ (ሔዋን) የሰይጣንን ምክር ተቀብላ ምን አደረገች?**

ሴቲቱ ዛፉ ለመብላት ያማረች እንደሆነች፣ ለዓይንም እንደምታስጐመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደሆነች አየች፤ ከፍሬዋም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው፤ እርሱም ከእርሱዋ ጋር በላ፤የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፤ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደሆኑ ዐወቁ፤ የበለሱንም ቅጠሎች ሰፍተው ዕርቃናቸውን ሸፈኑ (አገለደሙ) (ዘፍ.፫፥፮-፯)።

**<u>ጥያቄ</u>፦ ፍሬዋን በበሉ ጊዜ ዓይኖቻቸው ተከፈቱ ያለው ምን ማለት ነው?**

ከዚያ በፊት አዳምን ሔዋን መልካሙን እንጂ ክፉውን አያውቁም ነበር፤ ሰለዚህ ያልተፈቀደላቸውን ፍሬ በመብላት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለ ተላለፉ፣ ክፉ መሥራትና ክፉ ማየትን ዐወቁ ማለት ነው።

**<u>ጥያቄ</u>፦«እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደሆኑ ዐወቁ» ያለው ምን ማለቱ ነው?**

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፋቸው ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተራቆቱ ዐወቁ። ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ብርሃናዊ ጸጋ እንደ ተለያቸው ተገነዘቡ ማለት ነው።

**<u>ጥያቄ</u>፦አዳምን ሔዋን ትእዛዙን ከተላለፉ በኋላ እግዚአብሔር ምን አላቸው?**

እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ነውና በፊት እንደተናገረው በአዳምና በሔዋን የሞት ፍርድ ፈረደባቸው፤ የስይጣንን ሐስት ስምተው ትእዛዙን ስለጣሱ ረገማቸው፤ ከገነትም አስወጣቸው (ዘፍ.፫፥፱-፳፬)።

**<u>ጥያቄ</u>፦እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ከገነት ሲያስወጣቸው፣ እንደ ገና ወደ ገነት የሚመልሳቸው መሆኑን የሚያመለክት የነገራቸው የተስፋ ቃል ነበርን?**

መልስ፦ አዎን፤ ነበር፤ ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው፦

፩ኛ. እባቡን (ስይጣኑን) ሲረግም፣ «በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ (የሴቲቱ ዘር) ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ስኰናውን ትጠብቃለህ (ትነክሳለህ) የሚልነው (ዘፍ.፫፥፲፭)።

በዚሁ መሠረት፣ የሴቲቱ (የሔዋን) ዘር የተባለው በኋለኛው ዘመን አዳምንና ዘሮቹን ለማዳን ሲል እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን የሔዋን ዘር፣ የአብርሃምና የዳዊት ዘር ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ፣ በድንግልና ተወልዶ፣ ከኃጢአት በቀር ፍጹም ስው ሆኖ፣በፈቃዱ በመስቀል ተሰቅሎ በተቀበለው መከራና ሞት የቀደመውን ጠላት ሰይጣንን ድል አስርጐ፣ አዳምና ዘሮቹን ወደ ገነት መልሶአቸዋል።

፪ኛ. «ወይቤ እግዚአብሔር ናሁ አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ እግዚአብሔርም፣ እነሆ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አለ» (ዘፍ.፫፥፳፪)።

ይኸውም፣ አዳምን ለማዳንና ወደ ገነት ለመመለስ ከሥላሴ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ስው እንደሚሆን በቅድሚያ የተናገረ አምላካዊ ትንቢት ነው። በትንቢቱም መሠረት በኋለኛው ዘመን እግዚአብሔር ወልድ፣ ከድንግል ማርያም በድንግልና ተወልዶ በሥጋው ወልደ አዳም፣ ወልደ አብርሃም፤ወልደ ዳዊት ሲባል (ማቴ.፩፥፩-፲፯)፣ ከድንግል ማርያም የተነሳው አዳማዊና አብርሃማዊ ባሕርይ ባለመለወጥና ባለመከፈል፣ ከቃል ጋር ተዋህዶ አምላክ ሆኖአል።

፫ኛ. «መጽሐፈ ቀሌምንጦስና ገድለ አዳም» በተባሉ የትውፊት (የሥርዓት) መጻሕፍት እንደ ተመዘገበው ደግሞ፣ «እግዚአብሔር በቀጥታ በኋለኛው ዘመን ከልጅ ልጅህ ተወልጄ፣ ተሰቅዬና ሞቼ አድንሃለሁ» ብሎ ቃል ገብቶለታል።

**<u>ጥያቄ</u>፦አዳምንና ሔዋንን ያሳተ እባብ በእርግጥ ስይጣን ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለ?**

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ማስረጃ ይገኛል።

ለምሳሌ፦ «ወአርዌስ ዐቢይ ዘውእቱ ቀዲሙ ዘአስሐቶ ለኵሉ ዓለም ዘስሙ ስይጣን»፤ «ታላቁም እባብ (ዘንዶ) የተባለው ቀድሞ ዓለሙን በሙሉ ያሳተ ስይጣን ነው» ሲል ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል (ራእ.ለ2፥9)። እንዲሁም አዳምን ሔዋንን ያሳተ እባብ (ዲያብሎስ) በጌታችን መስቀል ከሥልጣኑ መሻሩንና ወደ ታች መጣሉን ሲያስረዳ፣ «አሁንም ለአምላካችን ማዳንና ኃይል፣ መንግሥትም ሥልጣንም ሆነ፤ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአል» ብሎአል (ራእ.፲፪፥፲)። የቤተክርስቲያን ሊቃውንትም በመጀመሪያ ዘመን ራሱ ስይጣን (ዲያብሎስ) በእባብ አካል ተሰውሮ አዳምንና ሔዋንን እንዳሳተ፣ ቃለ እግዚአብሔር ወልድም የእኛን ባሕርይ ገንዘብ አድርጐ ድኅንነትን እንደ ስጠን እንዲህ ሲሉ አስተምረዋል፤ «ወበከመ ኮነ እንከ ስይጣን በጕሕሉት ተኀብአ ውስተ ሥጋ ከይሲ፣ ከማሁ ኮነ ድኅነትነ እማእስር በተሰውሮተ ቃለ እግዚአብሔር በዘመድነ፤ ሰይጣን በተንኮል በሥጋ ከይሲ (እባብ) እንደ ተሰወረ፤ የእኛም ከፍዳ መዳናችን ቃለ እግዚአብሔር በባህርያችን በመሰወሩ፣ ሥጋችንን በመዋሐዱ (ሆነ)» ብለዋል (መቅ.ወን.አራተኛ ጉባኤ)።

ስይጣን በተንኮለኛው ፍጡር በእባብ ተሰውሮ አዳምንና ሔዋንን እንዴት እንዳሳተ መጽሐፍ ቅዱስ በሚለተለው መንገድ መዝግቦታል፤ «እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅተንኮለኛ ነበር። እርሱም ወደ ሔዋን ሄዶ፣ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።

ሴቲቱም (ሔዋንም) ለእባቡ ከገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ ሁሉ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለችው ከዛፍ ፍሬ እንዳንበላ እግዚአብሔር እንዳትሞቱ ከእርሷ አትብሉ፤ አትንኳትም ብሎ አ ዘዘን አለችው። እባቡም ለሴቲቱ (ለሔዋን) አላት፣ ሞትን አትሞቱም፤ ነገር ግን ከዛፍዋ በበላች ሁ ግዜ ዓይኖቻችሁ እንደሚከፈቱ፣ እንደ እግዚአብሔር መልካሙንና ክፉን የምታውቁ እንደም ትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ከዚህ በኋላ ሴቲቱ የእባቡን (የስይጣኑን) ምክር ስማች፤ ዛፍዋም ለመብላት ያማረች እንደ ሆነች፣ ለዓይንም (ለማየትም) እንደምታስጐመጅ፣ ለ ጥበብ መልካም እንደሆነች አየች፤ ከዚያም ከፍሬው (ከዛፍዋ ፍሬ) ወስደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ስጠችው፤ እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ፤ እነርሱም ዕራቁታቸ ውን እንደ ሆኑ (እንደ ተራቆቱ) አወቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ስፍተው ለራሳቸው ግልድም አደረ ጉ (አገለደሙ)» (ዘፍ.፫፥፩-፯)።

**<u>ጥያቄ</u>፦አዳምና ሔዋን ለምን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተው የስይጣንን ምክር ስሙ?**

እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ስው (አዳምን) ሲፈጥር የፈቀደውን መርጦ ለመያጥ፣ የፈለገውን መርጦለመውስድ፣ ወይም ለመወስን የሚያስችል ነጻ ፈቃድ ያለው ፍጡር አድርጐ ስለ ፈጠረው ነው፤ስለዚህአዳም ባለችው ነጻ ፈቃድ ምክንያት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቆ በሕይወት ከ መኖር ይልቅ የሰይጣንን ምክር ተቀብሎ የፈጣሪውን ትእዛዝ ተላለፈ፤ በመተላለፉም ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ተፈረደበት።

የመጀመሪያው ስው (አዳም) ነጻ ፈቃድ ያላት ለባዊት ነፍስ ያለችው ፍጡር ሆኖ እንደ ተፈጠረ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንዲህ ሲሉ አስተምረዋል፦ «ወገብረ ላቲ (ለነፍስ ሰብእ) ሥልጣነ በውስቴታ ትግበር በከመ ኀርየት እንዘ አልቦ ዘይኴንና ወዘይጌይላ፤ ከመ ይሁን ሠናይቲሃ ወእከ ያቲሃ በሥምረተ ኀሊናሃ በአምሳለ መላእክት»፤ እንደ መላእክት በኅሊናዋ ፈቃድ መልካምነት ዋና ክፋትዋ ከራስዋ ይሆንዘንድ ማንም የሚገዛትና የሚያዛት ሳይኖር፣ የወደደችውን እንድታደር ግ በውስጥዋ ሥልጣን (ነጻ ፈቃድ)አደረገላት» (መቅ. ወንጌል ፣ ሁሉተኛ ጉባኤ)።

ስለዚህ፣ የመጀመሪያዎቹ ስዎች (አዳምና ሔዋን) በገነት የተነገራቸውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቀው ቢኖሩ ኖሮ በኃጢአት አይወድቁም ነበር፤ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስም አይፈረድባቸውም ነበር፤ ነገር ግን ከላይ እንደ ታየው ሙሉ ነጻነት (ሙሉ ፈቃድ) ያላት ነፍስ ያለቻቸው ፍጡራን ሆነው ስለ ተፈጠሩ፣ በስይጣን ምክር ተመርተው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፉ፤ ከሕይወት ይልቅ ሞትን መረጡ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቀው በሕይወት ከመኖር ይልቅ ትእዛዙን ተ ላልፈውና የስይጣንን ምክር ተከትለው በሞት ጥላ ሥር መውደቅን መረጡ።

**<u>ጥያቄ</u>፦ የመጀመሪያው ኃጢአተኛ (ኃጢአትን መስራት የጀመረ) ማን ነው?**

የመጀመሪያው ኃጢአተኛ ስይጣን ነው።

**<u>ጥያቄ፦</u> ኃጢአት እንዲሠራ ሰይጣንን የመከረው ወይም ያስተማረው ማን ነበር?**

ሰይጣን ኃጢአት እንዲሠራ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንም አልመከረውም፤ ወይም ከማንም አላየም፤ ነገር ግን ከራሱ አመንጭቶ፣ ራሱ አስቦ ኃጢአትን መሥራት ጀመረ። የኃጢአት ጀማሪና መሥ ራች ራሱ ስይጣን ብቻ ነው።

ሰይጣን የመጀመሪያው ኃጢአተኛ ስለ መሆኑ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበረ አ ይሁድን ሲገስጽ፣ «እናንተ ካባታችሁ ከዲያብሎስ (ከስይጣን) ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ል ታደርጉ ትወዳላችሁ፤ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበር፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም። ሐስትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐስተኛ የሐስትም አባት ነውና» ብሎአል (ዮሐ. ፰፥፵፬-፵፭)።

**<u>ጥያቄ</u>፦ስይጣን (ዲያብሎስ) የሠራው የመጀመሪያ ኃጢአት ምን ነበር?**

የእግዚአብሔርን ህልውና መካድ ነበር። ሰይጣን ከራሱ አመንጭቶ፣ «እግዚአብሔር የለም» ብሎ ከመካዱም ሌላ፣ «እኔ ፈጣሪና እግዚአብሔር ነኝ» ብሎ በዐመጽ አምላክ (እግዚአብሔር) ለመሆን ሙከራአድርጐ ነበር። ስይጣን ፍጡር መሆኑን ክዶ ፈጣሪ ነኝ ስላለ፣ ፈጣሪውን ማመስገን ትቶ፣ «እመስገናለሁ እንጂ አላመስግንም» ስላለ ከክብሩ ተዋረደ፤ ከሥልጣኑም ተሻረ።

የስይጣንን መዋረድ አስመልክቶ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፤ እንዴት ከስማይ ወደቅህ? አንተ አሕዛብን ያዋረድህ ሆይ፤ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተወርወረህ ተጣልህ? አንተ ግን በልብህ ወደ ስማይ ዐርጋለሁ፣ ከስሜንም ዳርቻ በመስብስቢያ ተራራ በላይ እቀመጣለሁ፣ ከደመናዎች ከፍታ በላይ አርጋለሁ፣ በልዑልም እመሰላለሁ ብለህ ነበር። ነገር ግን ወደ ሲኦልና ወደ ጥልቅ ጕድጓድ ወረድህ» (ኢሳ.፲፬፥፲፪-፲፭)።

ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «በስማይም ስልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን (ሰይጣኑን) ተዋጉት፤ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፤ ነገር ግን አልቻላቸውም፤ ከዚያም ወዲህ በስማይ ስፍራ አልተገኘለትም። ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ስይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶእርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ፤ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ» (ራእይ.፲፪፥፯-፱)።

**<u>ጥያቄ</u>፦አዳምና ሔዋን በእባብ (በስይጣን) ምክር ተመርተው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለ ተላለፉ፣እግዚአብሔር ምን ብሎ ፈረደባቸው?**

መጀመሪያ እግዚአብሔር እባቡን እንዲህ ሲል ፈረደበት፤ «ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት፣ ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተረገምህ ሁን፤ በሆድህም ሂድ፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ አፈር ብላ፤ አንተም በሴቲቱ (በሔዋን) መካከል፣ በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነት አደርጋለሁ፤ እርሱ (የሴቲቱ ዘር) ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ስኰናውን (ሸሆናውን) ትነክሳለህ።» ቀጥሎም በሔዋን እንዲህ ሲል ፈረደባት፤ «በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛዋለሁ፤ በጭንቅም ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም አሳዳሪሽ ይሆናል።» በመጨረሻም እግዚአብሔር አዳምን እንዲህ ሲል ፈረደበት፤ «የሚስትህን ቃል ስምተህ ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍ በልተሃልና ባንተ ምክንያት ምድር የተረገመችትሁን፤ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ በድካምህ (በጣርህ) ከእርሰዋ ትበላለህ፤ ምድርም እሾህና አሜከላን ታበቅልብሃለች፤ የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ፤ ወደ መጣህበት መሬትም እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ (ላብህን እያፈስስህ) እንጀራህን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» (ዘፍ.፫፥፲፬-፲፱)።

ይህ በአዳም ላይ የተፈረደው የሞት ፍርድ፣ በአዳም የልጅ ልጅና በአዳም ዘር ላይ ሁሉ መድረሱን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «ኃጢአት በአንድ ስው ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአት ሞት መጣ፤ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአት ሰላደረጉ ሞት ለስው ሁሉ ደረስ» (ሮሜ.፭፥፲፪-፲፫)።አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፈው ያመጡት ሞት፣ እነርሱም ሆኑ ከእነርሱ ዘር የተወለዱ ነቢያት ሊያስወግዱት ወይም ሊሽሩት አልቻሉም። እንዲያውም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፣ ሁሉም በሞት ጥላ ሥር ወደቁ፤ ሁሉም ሞት ገዛቸው። እግዚአብሔር ይቅርታውና ምህረቱን የሚገልጽበት ዘመን በደረስ ግዜ ግን፣ ሞትን ሽሮ በሞት ጥላ ሥር የወደቁትን ያድን ዘንድ ከሥላሴ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከኃጢአት በቀር ፍጹም ስው ሆነ። ይህም በምስጢረ ሥጋዌ (ነገረ ክርስቶስ) ላይ በስፊው ተገልጿል።

ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ1991 ካሳተሙት የተወሰደ።